# መርሳትን ነው መርሳት

ከበልጅግ አሊ

በጨካኙ በአረመኔው የደርግ መንግስት በቀይ ሽብር ወቅት ከርቼሌ ወርጄ በነበረበት ወቅት አንድ እድሜ ልክ ተፈርዶበት የታሰረ እስረኛ ነበር።ይህ እስረኛ ሁል ግዜ እየደጋገመ ስለውጬ አለም ይጠይቀኝም ነበር። ከሁሉም የሚናፍቀው ኪንግ ጆርጅ ሻይ ቤትን ነው። እኔ ደግሞ ኪንግ ጆርጅ ሻይ ቤት የት እንደነበር  አላስታውሰውም። አንድ ቀን ታዲያ ጥያቄው ቢበዛብኝ „እኔ አላውቀውም ብዬሃለሁ ለምን ሁል ግዜ ደጋግመህ ይህንን ትጠይቀኛለህ“? ብዬ ጠየቅሁት። እሰረኛው እንደመደንገጥ ብሎ በምሬት ቃል „ታዲያ ምን ላድርግ ብለህ ነው የማውቀው እሱን ብቻ ስለሆነ ነውኮ„ አለኝ። በወቅቱ ስሜቱን የጎዳሁት ሰለመሰለኝ ብዙ ግዜ እፀፀት ነበር።

ይህንን ነገር አሁን ታዲያ በብዙ ሁኔታዎች መደጋገም ምክንያት እንደገና አሁን ላስታውሰው በቅቻለሁ። በኢሕአፓ አስቸኳይ ጉባዬና ከዛ በኃላ በኢሕአፓ ታሪክ ውስጥ የደረሰውን ታላቅ ክህደት በተደጋጋሚ ከልቤ አልወጣ ስላለኝ ደጋግሜ ያጫወትኩት አንድ ግለሰብ ለካ ሁኔታውን እንደኔ በጣም ያልተሰማው ኖሮ ጨዋታውን መደጋገሜን ቢያማርርብኝ እንደእስረኛው እኔም ምን ላድርግ ብለህ ድርጅቴን ፣ የልጅነት ፍቅሬን፣አካሌ የተቀጠቀጠበትን፣ስንት ጓዶቼን ያጣሁበትን እንዴት ልርሳው ብለህ ብዬ ነገርኩት።

በእውነቱ በኢሕአፓ ላይ የተሰራውን ክህደት የሚረሱት የኢሕአፓ የቀድሞም ይሁን የአሁን አባላቶች ካሉ የሚገርመኝ ይሆናል።እኔ በበኩሌ ይህንን ክህደት መርሳትን ለመርሳት ነው ቃል የምገባው። ምንም ቢባል ምን ይህ ታላቅ ክህደት በሃገራችን ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ ይነሳል። ከልጅ ልጅ እንዲተላለፍም ተፅፎም ሊቀመጥ ይገባል እንጂ ሊረሳ አይገባም። ምክንያቱም የተሰውቱን እንደገና ለመግደል የሚደረግን ጥረት እንዴት አድርጎ መርሳት ይቻላል።

ክህደት ለኢሕአፓ የመጀመሪያውም አደለም። የዘንድሮ ክህደት ግን ከሁሉም የሚለየው በኢሕአፓ ስም ለተደረገብን ጭፍጨፋ የአንጃው መሪዎች በኢሕአፓ ስም የተሰውትን ወክለው ይቅርታ ጠያቂ ለመሆን የሚያደርጉትን ያላሰለሰ ማጎብደድ ስመለከተው የክህደቱን ጥልቅነት ያሳስበኛል። እስከ አሁን በተለያየ ምክንያት ኢሕአፓን የካዱትን በሞላ ወደ ኃላ ስንመዝነው ይህንን ያህል ክህደት ያልታየ ስለሆነ የአሁኑ ክህደት በስፋቱም ይሁን በጥልቀቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሆኖ እናገኘዋለን።ሌላኛው ክህደት ደግሞ ሕብረ ብሔር ከሆነው ኢሕአፓ ወጥተው ዘርን በመጠቀም ደጋፊ ለመሰብሰብ (በአብዛኛውም ከኢሕአፓ የወጡት ባይሆንም በጣም በጥቂቶቹ በተለይም በአመረራር ላይ በሚገኙ) የሚደረገው የክህደቱ ሌላኛው ክፍል ነው። ይህ የዘር ጀርባ እየታዬ ድጋፍ መስጠት ወይም ደግሞ ደጋፊ መሰብሰብ  ኢሕአፓን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም እንደመካድ እቆጥረዋለሁ ። ለዚህም ዋቢዬን የነፀጋዬ ደብተራውን ጉዳይ ሲሆን ለስዬ ሲባል እንዳይነሳ የተከለከለው የነስዬን የዘር ምንጭ በሚጋሩ በጥቂቶች ገፋፊነት እንደሆነ ደግሞ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ብዙዎቹ የአንጃው መሪዎችና አንዳንድ የአንጃው አባላት ያንን የቀይ ሽብር ዘመን እንዳላለፉበትና የሌሎቻችን ስቃይን እንደማይሰማቸው እምናውቀው ሲገድሉንና ሲቀጠቅጡን ከነበሩት ጋር ለማበር ሲሉ ኢሕአፓነትን በመካድ የሚደርጉትን የማያቆርጥ ጥረት ልብ ብለን ስንመለከተው ምን ያህል የላሸቀ ስነልቦና ነው ያላቸው ብለን እንድንጠይቅ ይጋብዘናል።ዛሬ የአንጃው መሪዎች አብረዋቸው ከነበሩት የትግል አጋሮቻቸው ጋር ለመነጋገር ከሚያደርጉት ጥረት ይልቅ በብዙ እጥፍ ከኢሕአፓ ጠላቶች ጋር ለመተባበር የሚደርጉት ጥረት የጎላ ነው፡፡

በዚህ ሳምንት በአንጃው የፓልቶክ ክፍል በቀይ ሽብር የተሰውት የኢሕአፓ ወጣቶች ስም እዚህ ግቢ በማትባል አለብላቢት የደርግ ካድሬ ሲበከል አንዳንድ የአንጃ አባላት አበባ ሲረጩ ነበር። ሁኔታውን በቀይ ሽብር ወቅት ነፃ እርምጃ ለመውሰድ ከደርግ ጋር ከአበሩት አጃዎች ተግባር ጋር ይመሳሰል እንደነበር ያስታውሰኛል። ካድሬዋ „ለሰላሳ አመት ያጠፋችሁትን አምናችሁ አሁን ይቅርታ በመጠየቃችሁ ደስታዬ ከማንኛውም በላይ ነው“ በማለት ደርግ በቀይ ሽብር ኢሕአፓን ለማጥፋት ያደረገው ጥረት ትክክል እንደነበር

አስረግጣ ስትናገር ኢሕአፓ ነበርኩ የሚል ግለሰብ ይህንን እንዴት መቃወም እንደሚያዳግተው አይገባኝም። ይባስ ተብሎ ኢሕአፓ ያልነበሩ ሌሎች ግለሰቦች ሁኔታውን ሲቃወሙት አጃዎቹ ግን በፀጥታና አበባ በመበተን አድናቆታቸውን ለካድሬዋ መግለፃቸው የተሰዉትን ጓዶች እንደገና ለማጥፋት የሚደረግ ጥረት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ወያኔን ለማውረድ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ማበር አደለም እንደጥፋት የምቆጥረው። እንደ ክህደት የምቆጥረው የኢሕአፓ አባላት የአሁኑም ይሁን የቀድሞዎቹ ስለ ቀይ ሽብር አትናገሩ በሌላ ክፍል የተሰበሰቡት ይቆጣሉ እያሉ ታሪካችንን ለመርሳትና እኛም እንድንረሳው ለማድረግ የሚደርጉት የአንጃዎችን መቅበዝበዝ ስመለከት የአንጃው መሪዎች ከሆዳቸው በላይ ምንም የሚወዱት፣ የሚያከበርሩትና የሚኮሩበት አላማ እንደሌላቸው ነው የምንገነዘበው። ኢሕአፓነትን ወዶ ለኢሕአፓ ሲሉ የተሰውትን ጠልቶ ፣ እስር ቤት ያሉትን ክዶ እረስቶ ኢሕአፓነት የለም።

ሌላው ክህደት ደግሞ የተወዳጁ መሪያችንን የጸጋዬ ደብተራውን ስም አንስተው ከመወያየት የፀጋዬን አሳሪ፣ የዘንድሮ የባለ ቀን የብዙ ግዜ ባለሟል የሆነውን ወያኔ ስዬን ሲያወድሱ ሳይ ግልፅ እየሆነልኝ የመጣው ጉዳይ መታሰር፣ መገረፍ ፣መስቃየትን ብዙዎቹ የአንጃው መሪዎች እንደማያውቁት ነው።ያ ድምፅ ለሌለው ድምፅ ነን የምንለውን መርሆ አሽቀንጥረው ጥለው ለባለ ግዜና ሃብት በሙስና ላካበተ ድምጽ መሆን የጀመሩትን የአንጃው መሪዎች ይህንን ጉዳይ ቀደም ብለው ዴንማርክ በሚገኘው ወኪላቸው ቀድመው የጀመሩት መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ስዬ ከነ ፀጋዬ የተሻለበትና ዛሬ የተከበረበት ምክንያት ቢኖር ከሕብረ ብሄርነት ወደ ዘረኝት በሚደረገው ጉዞ በተነደፈው ንድፈ ሃሳብ መመሪያ በማድረግ ብቻ ነው።በዘር መለኪያ ካለሆነ እነ ፀጋዬ ከስዬ በማንኛውም መለኪያ ለአንጃዎቹ የሚቀርቡበት ጉዳይ አይኖርም።

ታዲያ የሚገርመው እውን ከእኛው ጋር በደርግ አካላቸው የጎደለ ፣ የእግራቸው ጠባሳ እስከ አሁን ያልጠፋ ፣ ስቃዩን ችግሩን የቀመሱት፣ አብረን ሆነን ዳግም ቀይ ሽብር ፣ እስራትና ስደት በሃገራችን እንዳይኖር እንታገላለን ብለን ቃል የገባን፣ እነ ፀጋዬ ይፈቱ ብለን አብረን የጮህን፣ ይህን ጉዳይ እውን አምነው ተቀብለው ነው በእነዚህ መሪዎቻቸው ላይ ምንም ተቃውሞ ሳያሰሙ የአሳሪ ፣ የገዳይንና የወያኔን ማስታወቂያ አዘጋጅ የሆኑት። እስኪ ለደቂቃ ወደ ኃላ ብላችሁ አስቡት የአሊ ሙሳን ፣ የመንግስቱን ፣ የመላኩን ስብሰባ እናንተ ወፌ ኢላላ በተሰቀላችሁበት ጊዜ ለትግሉ ይጠቅማል ብለው ሌሎች ጓዶቻችሁ ቢያነቡት ፣ የእናንተ ጥፍር ሲነቀል ፣ የእናንተ እግር ሲላጥ ፣ የእናንተ ብልት ጠርሙስ ሲንጠለጠልበት ፣ የእናንተን ጣት ከሰባዊ ፍጡርነት ውጭ ካለ ማደንዘዣ ሲቆርጡት፣ ሌሎች ጓዶቻችሁ የገስግስን ፣ የግርማ ከበደን፣የእርገጤ፣ ስብሰባ በሬዲዮናቸው ለህብረት ይጠቅመናል ብለው ቢያውጁ ምን ይሰማችሁ ነበር።እውን እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ፋሽሽት ግለሰቦች እናንተ የታሰራችሁበትን ቦታ ሳይናገሩ በእብሪተኝነት ዋስንግተን ውስጥ ስብሰባ ቢጠሩና በኢሕአፓ ስም የነበረ ራዲዩ ታላቁ መላኩ ተፈራ ሰለ ዴሞክራሲ ሊስረዳ መጥቶልና ውጡ ብሎ ቢቀሰቀስ ምን ትሉ ነበር። በእናንተ የተደረገው የነፀጋዬን አሳሪ ፣ አስሮ ፎካሪን ፣ የወያኔን ሚስጥር ጠባቂ የሆነውን ስዬ መካብና መስተዋወቅ እኔ እንደማየው መላኩ ተፈራን ወይም አሊ ሙሳን ስለዴሞክራሲ እንዲስረዱ መጠየቅና ለኢትዮጵያ ብዙ ጥሩ ቁም ነገር እንዳደረጉ ማስተዋወቅ ምንም የሚለየው የለም።በስው ቁስል እንጨት ስደድበት ካልሆነ በስተቀር።

እነ ፀጋዬ ባሉበት ወያኔ ይህንን ታላቅ የአንጃ ገድል ቀድቶ ስሙት ጓዶቻችሁ የሚሉትን ብሎ ቢያሰማቸው ምን ያስቡ ይሆናል ብላችሁ አስባችሁ ይሆን ይሆን። አዎ ዛሬ መሪዎቻችሁ ምክንያት እየፈጠሩ ዝም ሊያሰኙዋችሁ ይሞክራሉ። አዎ እኛ አደለንም እነርሱ ናቸው ብለው በሌሎች ለማሳበብ እንደጣሩ ተስምቶል። ግን እውነቱ በተከታታይ የምታዩት ነው። መሪዎቻችሁ የፓለቲካ መመፃደቅ አድርገው ሬዲዮው በኛ ቁጥጥር ስር አደለም ብለው ሲያውጁና ውሸት መሆኑን ስታውቁ ምን ያህል ባዶነት ይሰማችሁ ይሆን።ራዲዮውም በቁጥጥራቸው ስር ባይሆንም እንኳን ታዲያ ሁኔታውን መቃወም ምን ገዶ።ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም። ነገሩ መንግስቱን ለማስደሰት ለገሰ አስፋውን ማቀፍ ነው። ቅርበትን መግለፅ ነው። ኅበዝ ልብ እንበል።

ከዚህ በፊት በፃፍኳቸው ፅሁፎቼ ሁሉም ከደርጅቱ የወጡትን አንጃዎች ለማለት አልደፍርም ያልኩት አሁንም እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ቀኑ እየረዘመ ሲሄድ የአንጃው መሪዎች ለአላቸው የስልጣን ጥም ለዘመናት እናከብራቸው የነበረውን መርህዎች ሳባብረው ሲጥሉ ፣ በመካከላችን የነበረው የተሰው ጓዶቻችንን የማክበር ባህል ከአፈር ሲደባልቁ ፣

የታሰሩ እንደነ ፀጋዬ ደብተራው ያሉትን ጓዶች ስም ስዬና የዘር አጋሮቹ ይቀየማሉ በሚል እንዳይነሳ ሲከለከሉ ይህንን አለመቃወም ምን ማለት ነው። ዛሬ ብዙዎቻችሁ በእልክ ፈረስ ላይ ተሳፍራችሁ በወቅቱ እልካችሁ በወሰዳችሁ ድንገተኛ ደራሽ ላይ ተሳፍራችሁ ለዘመናት ቆመንለት የነበረውን መርሆ እየጣሳችሁ እስከመቼ እንደምትቆዩ እንድታስቡበት ላሳስባችሁ እወዳለሁ። ጠላቶቻችን ደግሞ እስከመጨረሻው ግበአተ መሬታችን ይቆፍሩልናል እንጂ አይተኙልንም። ዛሬ የእናንተ ወዳጅ ቢመስሏችሁ፣በጀርባችሁ በመሪዎቻችሁና በገዳዮቻችሁ ሕብረት የእናንተ ህልውናና ማንነት እየጠፋ በላዩ ላይ በሰለጠነ ፖለቲካ ስም በደማችሁ የፃፉችሁት ታሪካችሁ እየተፋቀ በቦታ የሰቆቃ ኑሮና የአድርባይነት አዲስ ታሪክ እየዋጣችሁ ነው።ይህንን ትቀበሉት ይሆን። ይህ የምሬት ቃሌ ስለሆነ ሊከብዳችሁ ይችላል።ግን ደግሞ እውነቱን ልብ ብላችሁ አጢኑት። እኔ በበኩሌ በአንዳንዶቻችሁ ላይ ተስፋ አልቆርጥም ታሪካችሁ ምንም ዛሬ ልደብቁት ብትሞክሩ ፣ በሰለጠነ ፖለቲካ በሚባል ዘይቤ ልታድበሰብሱት ብትጥሩ ፣ የአደጋችሁበት ለእውነት የመሞት ባህል ይቆይ እንጂ ብቅ ማለቱ አይቀርም ብዬ አመናለሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ የአንጃው መሪዎች ገና በጥዋቱ በመጀመሪያ የኢሕአፓ ጠላት የሆኑት ጋር ደጋፊ ለማግኘት ሄደው ሲቅበዘበዙ እንደነበርና አንዳንድ የደርግ ነፍሰ ገዳዮች የተሰበሰቡበትን ክፍሎች ደጋፊ ለማግኘት ጥርት አደርገው እንደነበር የሚታወቅ ነው። አሁን ደግሞ በየቦታው የኢሕአፓ ደጋፊዎችንና አባሎችን ለማነጋገር ጥረት እያደረጉ ነው። ይህ ታዲያ አንድ የኦሮሞኛ ተረት ያስታውሰኛል።

ይሆናል ቢሉን አህያ አረድን
አይሆንም ቢሉም አውጥተን ጣልን
ይሆናል ቢሉን ፈልገን አጣን ።

የአንጃው መሪዎች አንፈልግህም ያሉትንና ጥለውት የሄዱትን የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች አሁን በየሃገሩ እየሄዱ እንገናኝ የሚሉት ጉዳይ የሚሳዝን ነው።ኢሕአፓን ጥለው ሲሄዱ ያላማከሩትን ከዛም ከኢሰፓው ድጋፍ እናገኛለን ብለው አውጥተው የጣሉትን እንደገና ይሆናል ቢሏቸው መፈለጋቸው የሚገርም ነው።ዛሬ ና ተሰብስብ ቢሉና ቢጠሩት የሚሰማቸው አይኖርም። ሰምቶም ቢሄድ የነፀጋዬን ስም ለመጥራት የተፈራበትን ምክንያት የሚጠይቀው ቁጥሩ ብዙ ነው። የተሰው ጓዶችንና ዛሬ በወያኔ እስርቤት የሚሰቃዩ ጓዶቻቸው ያሁንም ሆነ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት ለአንጃው መሪዎች የስልጣን ጥም ብሎ የሚረሳ አይኖርም። የሚረሳ ቢኖር **ጭንብሉን አፍንጫው ጫፍ ላይ ደግኖ የሚናገረውን የማያውቅ ደደብ አጋሰስ ብቻ** ነው። ምን አልባት ይህንን እንደስድብ ትቆጥሩት ይሆናል ከሆነ ይቅርታ ይደረግልኝ። ለደሞክራሲ በሚደረገው ትግል የታሰሩ ግለሰቦች ታስረዋልና ስማቸውን መጥራት አያስፈልግም ብሎ የሚልን አጋሰስ ብል ስድብ ነው ብዬ አላምንም።ለነገሩ በፈሪነቱ መላው በገጠር የታገለ ሁሉ የሚውቀው ነው።

የዴሞክራስን ፣ የተደራጅቶ ትግል መማሪያውን ትምህርት ቤት ኢሕአፓን ለማፍረስ እየጣሩ ወደ ዴሞክራሲ የሚደረግ ጉዞ የማይምነት መንገድ የጨለማ ነው ሆኖ ያገኘሁት። በዚህ ከቀጠለ ደግሞ የሞቱት ከሞቱ በኃላ ፣ የታሰሩት ከተሳሩ በኃላ ይረሳ ከተባለ ፣ ማን ለመሳዋትነት እራሱን ሊቀርብ ነው ። ማንስ በቆራጥነት ተታግሎ እራሱን ለእስር ሊዳርግ ነው ? ይህ ሊታሰብበት የሚገባ ሲሆን ዋናው ግን መርሳትን መርሳት ሊሆን ይገባል። ለነፃነት የታሰሩትን መርሳትን ነው መርሳት እንጂ ለመርሳት መቸኮል ውጤት አይኖረውም።ትግሉ ከወያኔ ጋር ነው መቀጠል ያለበት ሲባል የወያኔን እድሜ ከግል የስልጣን ጥቅማቸው አንፃር ሁኔታውን እያስተካከሉ የሚያራዝሙትን አቁሙ ካልተባሉ የወያኔ እድሜ ወደድንም ጠላንም መርዘሙ አይቀርም።

የዛሬውና አያድርገውና የአንጃው ከፍተኛ መሪ በሁላችንም በሚከበሩበት ወቅት የተናገሩትን አሁን መልሼ ለእራሳቸው ላሳስባቸው እወዳለሁ። ያሉትን ቃል በቃል አስቀምጠዋለሁ።

„ አንድ ሰው ኢሕአፓን መስደብ ከጀመረ ወደ ወያኔ ሊገባ መሆኑን አትጠራጠሩ“

ብለውን ነበር።ታዲያ ዛሬ እሳቸው የአሉበት ሁኔታ ሌላ ስለሆነ ከእሳቸው ማብራሪያ እጠይቃለሁ።ሁኔታውን እንዴት ይመለከቱታል።ንድፈ አሳቡ በእርሶ ላይ ይሰራል ወይስ አይሰራም። የትንቢት ቀጠሮ ነውና ቀኑን እንጠብቅ።

**የትንቢት ቀጠሮ**

**እንዳይነጋ እንዳይመሽ ብልሃት ተገኝቶ**
**ጊዜውን መከላከል እንዳይቻል ከቶ**
**እንዲሁም በአለም ላይ አለ ብዙ ነገር**
**በዚያም ቢሉት በዚህ መሆኑ የማይቀር"።**

ከበደ ሚካኤል

1957

ድምፅ ለሌላቸው ድምፁን ለመስጠት የሚስብ በሰላም ይክረም!!!!!
በልጅግ አሊ